# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

ስልክ (Tel) +44 7937600756 ; +1 9168486790


## የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታና የሸንጎው የትግል አቅጣጫ

### የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ

ባለፉት 21 ዓመታት በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ የቆየው አምባገነናዊ ሥርዓት ቀስበቀስ እየጠነከረ በወጣው የአንድ ግለሰብ ብቸኛ አድራጊ ፈጣሪነትና የስልጣን ማዕከልነት ተሸብቦ እንደቆየ ሊያከራክር የማይችል እውነታ ነው። ለለጋሽ መንግስታት መስሎ ለመታየት ወደ ስልጣን ኮረቻው መቃረቢያ ላይ አንግቦት የነበረውን የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካዊ ሥርዓት አራማጅነት ባህሪ ውሎ ሳያድር አሽቀንጥሮ በመጣል፣ በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ፣ ግልጽ ሆኖ በሚታይ መልክ፣ በራሱ የስልጣን አምልኮት ዙሪያ የሚያጠነጥን የህወሓት/ኢህአዴግን ብቸኛ የአንድ ፓርቲን አምባገነንነት እየገነባ የነበረው መለስ ዜናዊ፣ ሰብስቦት የነበረውን የስልጣን ክምችት በትኖት እነሆ አልፏል።

መለስ ዜናዊ፣ የሀገሪቱን ሁለት ሶስተኛ የኢኮኖሚ አውታሮች፣ የሀገሪቱን መከላከያና የደህንነት ተቋማት፤ ዋና ዋና መንግስታዊ መዋቅሮችንና ተቋሞችን ሲቆጣጠር በቆየው በህወሓት ውስጥ በግለሰብ ፖለቲካ የበላይነት ይፈታተኑኛል ያላቸውን ከድርጅቱ በማባረርና የቀሩትንም ከስልጣኑ ማእከል በተለያየ መንገድ በማግለል፣ እራሱን ወደላይ በብቸኛነት ማውጣቱ ይታወቃል። ወደአምልኮ ደረጃ እንዲደርስም የሚያመቻቹ ተከታዮችን በራሱ ዙሪያ ሰብስቦ እንደነበር አይሳትም። ምንም እንኳ ህወሓት/ኢሕአዴግ የመለስ መሞት የፈጠረውን ክፍተትና በውስጡ ያስነሳውን የስልጣን ሹኩቻ ዝቅ አድርገው ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት ከነሱ የሚጠበቅ ቢሆንም፣ በመለስ ዜናዊ ወደ ዳር ተገፍተው የነበሩ የህወሓት የፖለቲካ ሃይሎች እራሳቸውን እንደገና ቦታ ለማስያዝና ስልጣን ለመቀራመት ከሚያደርጉት ሩጫ ጀምሮ፣ እስከ የሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅት ተብየ መሪዎች ድረስ መለስ በብቸኛነት ይዟቸው የነበሩትንም ሆነ በመለስ ታማኞች ተይዘው የነበሩ ከፍተኛ የመንግስትና የተቋም ስልጣኖችን ለመቀራመት በይገባኛልነት ፍጥጫና ፍትጊያ ውስጥ ኢህአዴግ መነከሩ ግልጽ ነው።

የኢሕአዴግ እምብርት ሆኖ በቆየው ህወሓት ውስጥ የመለስ መሞት በስልጣን ረገድ የፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት በውስጥ በሚደረገው መገፋፋትና የርስ በርስ መራኮት፤ ድርጅቱ የሀገሪቱን ኢኮኖሚና ወታደራዊ ክፍሎች በመቆጣጠር አሁንም የበላይነቱን እንደያዘ ቢሆንም፤ ከፖለቲካ አንጻር ግን በኢህአዴግ ውስጥ ያለውን ሚዛን ዝቅ እንዲል ያደረገበት ሁኔታ እውን ሆኗል። ይህ ሁኔታም በህወሓት ዙሪያ ተሰባስበው ከነበሩትና ነባር የሥርዓቱ ገንቢዎች ፍላጎት ውጭ መለስ በምክትልነት አስቀምጦት የነበረውን ሀይለማርያም ደሳለኝን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲያስቀምጥ፤ ደመቀ መኮንንን በምክትልነት እንዲቀመጡ አድርጓል። እነዚህ ሰዎች እስከዛሬ ድረስ በህወሓት ቁጥጥር ሥር በነበረው ስርዓትና የአገሪቱ የሥልጣን መዋቅር ላይ ምን ያህል እውነተኛ የሥልጣን ሃይል ሰጥቷቸው ሀገሪቱን በሚመስላቸው መልክ ሊመሩና ሊቆጣጠሩት እንደሚችሉ አጠያያቂና በቅርቡም የምናየው ይሆናል። ነገር ግን እስካሁን እንደታየው ከመለስ ዜናዊ ጥላ ስር ሊወጡ ያልቻሉበትና ከራሳቸው በላይ መለስን መስለው ለመቅረብ ጥረት የሚያደርጉበት፣ "በታላቁ መሪ" ጥላ ሥር ያሉ እንደሆኑ የሚለፍፉበት፤ መለስ ቢሞትም መለስ ሲመራው የነበረው የአንድ ፓርቲ አምባገነን ስርዓት ለማስቀጠል የሚምሉና የሚገዘቱበት፤ መለስ ሲያካሂድ የቆየውን የፖለቲካ ድርጅቶችን የማንገላታቱንና የማዋከቡን ሥራ የቀጠሉበት ሁኔታ ነው ያለው።

በኢኮኖሚ ረገድም ከቁጥጥር ውጭ የወጣ የዋጋ ግሽበትና በዚህም ምክንያት እየተባባሰ የመጣዉ የኑሮ ውድነት፤ እንዲሁም ሥራ አጥነትና ድህነት ሕዝቡን እጅጉን እያማረረውና በቀን አንዴ መመገብ የተቸገረበት፣ በጥቂት ሃብታሞችና ዕለት ተዕለት መኖር ባቃተዉ በብዙሃኑ ሕዝብ መሐል ያለው የገቢና የኑሮ ደረጃ ልዩነት እጅጉን መስፋትና የሙስና መሰራጨት ሕዝቡን እጅጉን እየተፈታተነ ያለበት ሁኔታ ነው በሀገራችን እየቀጠለ ያለው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም የመናገር፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቱ እጅጉን እንደተገደበበትና ሰብዓዊ መብቱ ተረግጦ ከፍርሃትና ስጋት ጋር እየተፋለመ ለመኖር መገደዱ እንደቀጠለ ሲሆን፤ የመብት ረገጣው የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችንና የነሱን




Tel. : +44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com

አባላትና ደጋፊዎች፤ ጋዜጠኞችን፣ ከማንገላታትና ከማዋከብ አልፎ፤ የእምነት ተቋሞችን መዳፈሩን በማጠናከር፣ ዛሬ በእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ የሚደርሰው ዓይን ያወጣ የሙብት ረገጣ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

በነጋዴው ላይ የተዘረጋው የዘረፋ ግብር ከአቅሙ በላይ እያሻቀበ ሲሆን፣ በምሬትም ንግዱን እየዘጋ የሚሄደው ነጋዴ ቁጥር እየጨመረ ነው። በተቃራኒው እንደ ኤፈርትን አይነት በህወሓት ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ያሉ የንግድ ተቋማት፣ ገደብ የለሽ የውጭ ምንዛሪና የገበያ ድርሻ እየተሰጣቸው፣ ከግብር ነጻ ሆነው ከውጭ እቃ እንዲያስገቡና እንዲንቀሳቀሱ እየተደረገ፣ ሌላውን ነጻውን ነጋዴ እያቆረቆዙ፣ የፍትሕ ያለህ በሚያሰኝ ሁኔታ የሃገሪቱን ቁልፍ የሆኑ ኢኮኖሚ ክፍሎችን በሞኖፖሊ እንዲይዙ የተደረገበት ሁኔታ ላይ ነው አሁንም ሀገሪቱ ያለችው።

በገበሬዉ ላይ ከማዳበሪያ መከልከል እስከ መሬት ያላአግባብ መነቀል፣ የሙብት መጣስ ተቃውሞ ጥያቄ በማንሳቱ ከመታሰርና ከመደብደብም አልፎ እስከ መገደልም የሚያደርስ በደል የሚፈጸምበትና የተማረረው የገጠር ሕዝብ ብሶቱን ከከተሜው ጋር በእምርታ የሚያሳይበት ጊዜ እየደረሰ ነው። የከተማው ነዋሪ በከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ንብረቱን በግፍ ከመነጠቁ አልፎም፤ በየጊዜው ያላግባብ ከመኖሪያው የሚፈናቀልበት፣ አራስ ወልዳ የተኛችበት መኖሪያ ቤቷ ሳይቀር በጠራራ ፀሓይ የሚፈርስበት ምድር ሆናለች፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እስትንፋስ እንዳያገኙ ያለማቋረጥ በህወሓት/ኢህአዴግ የማያቋርጥ ጫናና ወከባ፣ እስራትና እንግልት እየተደረገባቸው ቢሆንም፤ ያላቸውን አቅም ለማሰባሰብና አንድ ብሄራዊ የሆነ ህብረት በመፍጠር ለህዝብ ተስፋ ለመሆን እስካሁን አለመቻላቸው አሳሳቢ እንደሆነ ነው። አገዛዙ በሚያደርገው ከፍተኛ አፈናና ሽብር ምንም ጠንካራ ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ እንዳይፈጠርና እንዳያንሰራራ ባለ በሌለ ሃይሉ ብዙ ባጀት መድቦ በመስራት ላይ ይገኛል። ሆኖም ግን፣ በአንፃሩ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ደግሞ፣ ያለምንም ፍራቻና ተፅዕኖ፣ በነፃ የመናገር የመሰብሰብና የመደራጀት ነፃነት እያላቸው፣ በቅጡ መደራጀት ባለመቻላቸው፤ ያላቸውን የአቅም፣ የዕውቀት፣ የገንዘብና የተለያየ ጫና የማሳደር ኃይል በአግባቡና በበቂ አልተ ጠቀሙበትም።

## ኢትዮጵያና የውጭ ኃይሎች

ምዕራባውያን መንግሥታት ምንም እንኳን በሀገራችን ያለው አገዛዝ ጸረ-ዴሞክራሲያዊ እንደሆነና በህዝብ ላይ ቀጣይ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ገፈፋ እንደሚያካሂድ ሙሉ በሙሉ ቢያውቁም፣ በስልጣን ላይ ካለው ቡድን ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያዩትና የሚተልሙት በቅድሚያ ከራሳቸው ጊዚያዊ ጥቅም አንፃር እንጂ ከኢትዮጵያና ከሕዝቧ ዘላቂ ጥቅም አንፃር እንዳልሆነ በግልጥ አሳይተዋል። ለምዕራባውያን መለስ ዜናዊ የአካባቢው ፀጥታና ጥቅም አስካባሪያቸው በመሆን ያገለግላቸው ስለነበር፣ የእነሱ ጭንቀት ከመለስ ሞት በኋላ አገሪቷና አካባቢው ሳይበጠበጥ ነገሮችን እንደበፊቱ ሊያስቀጥል ወደሚችል ሥርዓት ያለ ብዙ ግርግር መሸጋገር መቻሉ ብቻ ሆኗል። በዚህም ምክንያት የእነርሱ መመዘኛ እንደ ሌሎች አፍሪካውያን አገሮች የሥልጣን ሽግግሩ ሌላ ተጨማሪ ብጥብጥ ሳይፈጠር ለኃይለማርያም ደሳለኝ ተላለፈ በሚል ያለው ጨቋኝ ስርዓት እንዳለ እንዲቀጥል መሆኑን እንደ አንድ ትልቅ እርምጃ ነው የቆጠሩት። በዚህ በጥቅም ብቻ በታወረዉ አመለካከታቸው ላይ ተመስርተው አፋኙን የህወሓት/ኢሕአዴግ ስርዓት ለሁለት አሰርት ዓመታት በሕዝባችን ጫንቃ ላይ ተንሰራፍቶ እንዲቆይ እስካሁን ያስቻለውን የተለመደ የገንዘብ ድጎማቸውንና የዲፕሎማሲያዊ እውቅና አሁን በውስጥ የስልጣን ሽኩቻ እየታመሰ ላለው አምባገነን ቡድንም መስጠት፤ ቀጥለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቻይና በአፍሪካ የኢኮኖሚ ግንኙነቷን ለማስፋት በምታደርገው መሯሯጥ በሀገራችን ያለውን የአንድ ፓርቲ አምባገነን አገዛዝ በቀጣይነት ለመርዳት ቁርጠኛ ሆና ተነስታለች፤ የእርሻ መሬቶችን ከሚቀራመቱት አገሮችም አንዷ ሆናለች። የሸቀጥ ምርቶቿን ለማራገፍም ትልቅ ገበያ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገችም ነው።

ህንድ፣ ሳውዲ አረብያ፣ ግብጽና መሰል የውጭ መንግስታትም የሀገሪቱን ግዙፍ ድንግልና ለም መሬቶች በዝቅተኛ የኪራይ ክፍያ እስከ 99 ዓመት ደረስ በመከራየት የሀገሪቱን ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች ከመኖርያና ከመንቀሳቀሻ ቦታቸው በግፍ እያፈናቀሉ ይገኛሉ። የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥትም የሀገሪቱን መሬቶች ለውጭ አሳልፎ በመስጠት የሚያገኘውን ገቢ የውጭ ምንዛሬ ችግሩን ለመቅረፍ እየተጠቀመበት ይገኛል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ የተንሰራፋው ሙስና ታይቶ ከማይታወቅበት ደረጃ እንዲደርስ አድርጎታል።

## የሸንጎው ግቦች – ከየት ወዴት?



*Tel.* : +44 7937600756 , +1 9168486790 *E-mail* : shengo.derbiaber@gmail.com

በሀገራችን ያለውን አጠቃላይ ችግር ከተመለከትን፣ የተቃዋሚው የጋራ ግብ ምን መሆን አለበት በምንስ ዙሪያ አንድ ላይ መምጣት አለበት የሚለውን መመለስ ያስፈልጋል። በሸንጎው በኩል የጋራ ግባችን፤-

ህዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤትነቱ የሚያረጋግጥባት፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፤ዜጎች በእኩልነት፤ በመፈቃቀድና በመተሳሰብ አብረዉ የሚኖሩባት፤ ሀገራዊ አንድነቷ የተረጋገጠባት፤ የብሄሮች ባህል፤ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች የሚከበሩባትና የሚበለጽጉባት፤ የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓትና ተሳትፎ የሚረጋገጥባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረት ነው።

ከላይ ወደተጠቀሰው ግባችን ላይ ለመድረስ ደግሞ፤

1. ከላይ ያለውን ግብ የሚጋሩ ሁሉ በአንድ ላይ መሰባሰብና ጠንካራ የፖለቲካ ኃይል መፍጠር አለባቸው፣

2.በተባበረ ኃይል ዛሬ በሃገሪቱ ላይ የሰፈነውን ዘረኛና ጸረ-ዴሞክርሲያዊ ሥርዓት ማስወገድ፤ ሥርዓቱን በማስወገድ የታገሉት ሃይሎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ሌሎችም የሕብረተሰቡን ሰፊ ተሳትፎ አመላካች ሊሆኑ የሚችሉ ክፍሎችን በሙሉ ያሳተፈ ብሄራዊ እርቅንና መግባባትን ግቡ ባደረገ ሂደት የሽግግር መንግሥት ማቋቋምና የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም:-

ሀ. አዲስ ሕገ-መንግሥት እንዲረቀቅና በህዝብ እንዲጸድቅ ማድረግና

ለ. በሕገመንግሥቱ በሚፈቀደው መሰረት በሐገሪቱ ነጻና ፍትሃዊ የሆነ ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ፤ ሕዝብ ከሚቀርቡለት አማራጮች ያለማንም ጣልቃ ገብነት መሪዎቹን በነጻ መርጦ እንዲሾም ማስቻል።

***ወደግባችን ለመድረስ የተቃዋሚ ሃይሎች የመደራጀትና የመሰባሰብ ወሳኝነት***

ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ለውጦ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፣ በሀገር ቤትና ከሀገር ውጭ የተጠናከረና የተቀናጀ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል። በሀገር ቤት የተደራጀ ህዝባዊ ትግል በማድረግ ያለውን አምባገነን ሥርዓት ከውስጥ መታገልና መነቅነቅ የሚያስፈልግ ሲሆን፤ በውጭ ደግሞ የተጠናከረና የተቀናጀ ዲፕሎማሲያዊና ተዛማጅ ትግሎችን በማድረግ የሥርዓቱን የፋይናንስና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፉን ማድረቅ ያስፈልጋል። እነዚህን ሁለት የትግል ዘርፎች በውል ለማድረግ ደግሞ በበቂ መደራጀትን ይጠይቃል። በይፋም ይሁን በኅቡእ ተደራጅተው የሚታገሉ የፖለቲካ ሃይሎች፣ እነዚህን ሁለት የትግል ዘርፎች አጣምረው መታገል ይጠበቅባቸዋል። በማደራጀትም ረገድ በሀገር ቤትም ይሁን፤ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን የማደራጀት ሃላፊነት አለባቸው።

በሀገራችን ያለውን አስከፊ ስርዓት ለማስወገድ የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በቁጥራቸው ከሚፈለገው በላይ የበዙ መሆናቸውን ማንም የሚስተው አይደለም። መብዛታቸው በራሱ የሚፈጥረው ችግር ባይኖርም፤ የዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ተፈጥሮ ህዝብ ያለምንም ጣልቃ ገብነት የሚበጀውን መምረጥ የሚችልበት ሁኔታ ባልተሟላበት ሁኔታ ግን፤ የአጭር ጊዜ መርሃ ግብራቸው በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መፍጠር የሆኑ ኃይሎች ተነጣጥለው መቀጠላቸው የሚፈለገውን ስርአት ለመፍጠር የሚደረገውን ትግል የሚጎትትና የሚጎዳ መሆኑን ያለፉት 21 ዓመታት ተመክሮ ያሳያል።

የተቃዋሚ ሀይሉ በአንድ ላይ በመሆን ካወቀበትና ሁኔታዎችን በአግባቡ አጢኖ ሊይዝ ከቻለና፣ ከስሜታዊነት፣ ከጀብደኝነት፣ ግትርነት፣ ተጠላላፊነት፣ ቡድናዊነት (ወገንተኛነት)፣ ከትምክህተኝነትና ጠባብነት የፀዳና የሰከነ የወቅታዊ ሁኔታ ትንታኔዎችን ማድረግ ከቻለ፣ በአግባቡም የትግል ስልቱን ከነደፈ፣ በመለስ እግር ሊቀጥል የሚፈልገው፤ አምባገነኑ ሥርዓት እየተዳከመ ሄዶ፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሻለ ሁኔታ መፍጠር፤ ለሕዝብ የስልጣን የበላይነት በር መክፈት ይቻላል።

በሸንጎው ዕምነት ለሥርዓት ለውጥ የምናደርገው የመጀመሪያው መሠረታዊ እርምጃ አንጥረን ባወጣናቸው የጋራ ራዕይና ዓላማዎች ዙሪያ በውጭ የሚገኘው የተከፋፈለና የተዳከመው ሠፊውን ህዝባዊ የተቃዋሚ ጎራ አንድ ላይ በማሰለፍና በማቆም በሚፈጠረው የትግል ኃይል፣ በአገር ውስጥ የሚፈለገውን የሕዝባዊ እምቢተኝነት የትግል ማዕበል እንዲፈጠር ማገዝና ማበረታታት ይቻላል።

ይሄንን የምንፈልገውን በሠፊውና በቅጡ የተደራጀ በውጭ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ የተቃዋሚ ጎራ ለማምጣት፣ በተቀዳሚነት እንደ ዕንቅፋት የሚነሳው የተደራጀው የተቃዋሚ ኃይሎች በአንድ ላይ ለመቆምና ለመስራት ያለመቻል ነው። በተወሰነ ደረጃ ይሄ ክስተት ዕውነተኛነት እንዳለው ሆኖ፣ ሸንጎው ይሄንን ችግር ለመቅረፍ የተወሰነ አመርቂ እርምጃዎችን መጓዙን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ ደግሞ በጣም ሊሰመርበት ይገባል። ለዚህም ሸንጎው በራሱ ውስጥ ግለሰቦችን እና የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶችን ማሰባሰቡ ብቻ



*Tel.* : +44 7937600756 , +1 9168486790 *E-mail* : shengo.derbiaber@gmail.com

ሳይሆን፤ በተለያየ ምክንያት ሸንጎውን ካልተቀላቀሉትም ጋር በቀጣይነት በመተባበር በጋራ የትግል እንቅስቃሴዎችን ለማካሄድ እንዲቻል ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይም ይገኛል።

ሸንጎው የቀረፃቸው አንኳር መርሆዎችና ዓላማዎች አብዛኛውን ተቃዋሚ ሊያሰባስብ ይችላል ብሎ ያምናል። ሸንጎው የመስራች ጉባኤውን ካካሄደ በኋላ በጉባኤው ካልተገኙት ጋር እንደገና ለመሰባሰብ ባደረገው ጥረት፣ በነዚህ ዓላማዎች ዙሪያ አብዛኞቹ ልዩነት እንደሌላቸው ለመገንዘብ ችሏል። ነገር ግን አንዳንዶቹ ወሳኝ ባልሆኑ የአሠራርና የአካሄድ አስተሳሰቦች ልዩነት ብቻ አብረው ለመቆም እንደተሳናቸው በቀላሉ ሊታይ የሚችል ሆኗል። ስለዚህ ሸንጎው በአንድ በኩል የቀረፀውን ራዕይና ዓላማዎች ለሕዝብ ለማስተዋወቅና በዙሪያውም እንዲሰባሰቡና እንዲደግፉ በተቀዳሚነት እየሰራ ሲገኝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከሸንጎው ጋር መሠረታዊ ልዩነት ከሌላቸው ከጅምሩ አብረው ሊቆሙ ካልቻሉ ኃይሎች ጋር ከጋራ እንቅስቃሴም በላይ፣ በጣም በተቀራረበና በተቀናጀ መልክ ለመታገል ጥረት ማድረጉን ይቀጥላል።

## የውጭ ጉዳይና የዲፕሎማሲ ምልጃ

ከዚህ ሌላም በተለይ በውጭ የሚደረገው ትግል ዋንኛው ከሆኑት መካከል የውጭ ጉዳይና የዲፕሎማሲው ትግል እንደመሆኑ፤ ድምፅ ለተነፈገው ሕዝባችን እንደ አምባሳደር በመሆን ድምፁን ማሰማትና የሚደርስበትን አፈና፣ ግፍና ጭቆና ለዓለም መንግሥታትና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የማቅረብ ትልቅ ሃላፊነትን ያጠቃልላል። ሸንጎው ከዚህ አንፃር በግል ከፈጠራቸው ግንኙነቶች በተጨማሪ ከሌሎች ጋራ በአንድ ላይ በመሆን የበለጠ ውጤታማ የሆነ ሥራ ለመስራት ጥረት እያደረገ ይገኛል። በተለይም ለኃያላኑ መንግሥታት በሥልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መደገፍ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የሕዝብ አመኔታ የሌለውን አምባገነናዊ ቡድን በሥልጣን ላይ እንዲቆይ ለጊዜው የሚረዳ ቢሆንም፤ ለወደፊቱ በዘላቂነት ሰላምና መረጋጋት ባገራችን ብቻ ሳይሆን በአካባቢውም ጭምር እንዳይኖር የሚያደርግ አርቆ ያላሰበ አካሄድ መሆኑን በተደጋጋሚ ማስገንዘብና ማጋለጥ እንደሚያስፈልግ በማመን ይሰራል። ይልቁንም በእነሱ ድጎማ ነፍሱ ያለውን አገዛዝ የሚያዳምጣቸው ከሆነ፤ የሰው ልጅ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚፃረር ድርጊቱን እንዲያቆም፣ የኢትዮጵያውያን የመናገር የመሰብሰብና የመደራጀት መብት ሙሉ ለሙሉ እንዲያከብርና፣ በአገሪቱ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሁሉንም የተቃዋሚ ሃይሎች የሚያሳትፍ የሰላምና የዕርቅ የሽግግር ሂደት የሚመጣበትን ጎዳና እንዲከተል እንዲመክሩት፣ አለበለዚያ ግን እንደ አሁኑ ለዚያ ፍቃደኛነቱን የማያሳይ አካሄድ የሚከተል ከሆነ፤ አገዛዙ ለራሱም፣ ለአገሪቱም፣ ለአካባቢውም አለመረጋጋትና አደጋ ውስጥ መውደቅ ተጠያቂ እንደሚሆን እንዲያሳስቡት በተደጋጋሚ ማስገንዘብ እንደሚያስፈልግ በማመን ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

በሸንጎ እምነት፤ የተቃዋሚ ኃይሉ ከበረታና በአንድ ድምጽ ከቆመ፣ የህዝቡ ትግልም ከጎለበተ፣ እንዲሁም፣ የምዕራቡ ሃይል ከፍተኛ ጫና ሊያሳድር ከቻለ፣ ለውጥ ለማምጣት ዕድሉ ሊሰፋ ይችላል። የተቃዋሚ ሃይሉ መተባበርና አማራጭ ሆኖ መቅረብ የምዕራብ ሀገራትን የማሳመን ጉልበቱ እንዲጨምር ማድረጉ ጥርጥር አይኖረውም።

## ቀጣይ አቋሞችና ጥሪዎቻችን

1. ***<u>ተቃዋሚውን በተመለከተ</u>***

ሸንጎ የጋራ አገራዊ ችግሮችን በጋራና በመተባበር ለመፍታት ይቻላል የሚል ጽኑ እምነት አለው፤ ስለሆነም በተቃዋሚው መሃል ሊኖር ይገባል ለሚለው የህብረት ስራ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ያለመታከት ይሰራል፤

- ሸንጎ የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት ይሆን ዘንድ፤ የተቃዋሚው ክፍል በየጊዜው ወቅታዊ ሁኔታዎችን በርጋታ በመተንተን፤ ከገዥው ፓርቲ የሚለየውን የጠራ አገራዊ ራዕይና የፖለቲካ ግንዛቤ ኖሮት የትግል አቅጣጫውን እንዲቀይስ ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል፣
- የኢትዮጵያ ህዝብና የተቃዋሚ ኃይሎች ህወሓት/ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በህዝባችን ላይ የሚያደርሰውን ረገጣና ማሰቃየት አክትሞ ለዘላቂ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ የሚበጅ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች ሊያሳትፍ የሚችል፣ ብሄራዊ እርቅንና መግባባትን ግቡ ያደረገ ሂደት እንዲጀምር፤ሸንጎው ይጥራል፣
- ሸንጎ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ትግልና ግንባታ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው የገንዘብና ሌሎች የአቅም ግንባታ ግብአቶች ሲሳኩ ነው ብሎ ስለሚያምን ለጋራ ሃገር የሚቆረቆሩ ሁሉ ቋሚ አስተዋጾ እንዲያደርጉ ከሌሎች ጋር በመተባበር የአቅም ግንባታ እቅድ አውጥቶ ከስራ ላይ ያውላል፣ ሃላፊነት ያለው ሪፖርት በየጊዜው ለሕዝብ ያቀርባል፣



*Tel.* : +44 7937600756 , +1 9168486790 *E-mail* : shengo.derbiaber@gmail.com

- ሸንጎ፤ የትግሉ ማእከል ኢትዮጵያ፤ የትግሉ ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ያምናል። ሆኖም ግን በውጭ አገራት ያሉ የትግል እንቅስቃሴዎች በሀገር ቤት የሚካሄደው ትግል አካል ነዉ ብሎ ስለሚያምን፣ በሃገር ቤት ሊኖር በሚችል የመስዋእትነትና የትጋት ደረጃ ትግሉ እንዲጠናከር ልዩ ጥረት ያደርጋል፣
- ሸንጎ በሀገር ቤት ውስጥ በይፋም ሆነ በኅቡእ ከተደራጁ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ጠንካራ ድርጅታዊና ፖለቲካ ስራውን በከፍተኛ ደረጃ ያጠናክራል።

2. <u>ሕዝባችንን በተመለከተ</u>

- ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንኳን ለለውጥ ዝግጁ መሆኑንና መስዋዕትነትም ለመክፈል የማይመለስ እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያቶችና አጋጣሚዎች ያሳየ ቢሆንም ለድል የሚያበቃ አመራርና የተጠናከረ ሃይል ሊያገኝ አልቻለም።
- ሸንጎ ለህዝቡ አቅጣጫና አመራር ሊሰጥ የሚችል ሠፋ ያለ ጠንካራ የተባበረ ሀይል ተጠናክሮ እንዲወጣ ተቃዋሚ ሃይሎች በሙሉ ልብ እንዲሰሩና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጥሪውን በያሉበት እንዲደግፉ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፤
- ሸንጎው ህዝቡ በያለበት በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ በሚያመቸውና በሚመስለው ተደራጅቶ ለመብቱ እንዲታገል፣ ትግሉንም እንዲያስተባብርና እንዲተባበር ይጥራል ያበረታታል።

3. <u>ህወሓት/ኢህአዴግን በተመለከተ</u>

- ሸንጎ የህወሃት መሪዎችንና ተከታዮችን ለያይቶ በማየት፤-

⁕በኢትዮጵያ የተንሰራፋው አምባገነናዊ አገዛዝ እንደ ስርዓት በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን በደል በማስረዳት ከህዝቡ ጎን እንዲቆሙ ያለመታከት ጥረት ያደርጋል፣

⁕በአምባገነኑ ስርአት ተደግፈው፤ ግፍ የሰሩ መሪዎች በሃገርም ሆነ በአለም ተቋማት ለፍርድ እንዲቀርቡ ይጥራል። ጠቃሚ የሆኑ መዝገቦችን፤ ማስረጃዎችን መሰብሰብ፤ ተባባሪ የሚሆኑ አለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶችን ያበረታታል፤

⁕ሸንጎ በህወሓት/ኢህአዴግ አባልነት መመዘኛ ብቻ የወደፊት ቂም በቀልና የመሰረታዊ መብቶችን የሚነፍጉ እርምጃዎችን ይቃወማል

4. <u>የምዕራቡን ሀይል በተመለከተ፤</u>

የተቃዋሚ ሃይሎች በጋራ ካልሰራንና ለምእራቡ አለም በአንድነት እንደቆምን ማሳየት ካልቻልን፤ ኢትዮጵያ የመከፋፈልና ለአካባቢውም የሚተርፍ የመበጣበጥ እድል ሊገጥማት ይችላልና ምእራቦችን በአንድ ድምጽ የምንቀርብበትን ሁኔታ ማቀናበር፣ ማጠናከር።

ሸንጎ፤ የተቃዋሚው ሃይል ከላይ የተጠቀሱትን ግቦች በስራ ለመተርጎም ከቻለ፣ የምዕራቡ ሀይል ለራሱ ዘላቂ ጥቅም ሲል በራችንን በማንኳኳት ጆሮውን እንደሚሰጠን አያጠራጥርም። ሆኖም፤ ያለፉት ሃያ አንድ አመታት ያስተማሩን የተቃዋሚው ሃይል ድክመት፤ መከፋፈል፤ ለሃገራዊና ዲሞክራሲያዊ አማራጭ በአንድ ላይ አለመቆም፤ በአንድ ድምጽ አለመናገር፤ በምእራብ አገሮች፣ በተለይ፤ በአሜሪካና በአውሮጳ የጋራ ማህበር ተሰሚነትን፤ ተቀባይነትን፤ አመኔታን ለማግኘት አላስቻለውም። በአንድነት መቆማችን አንዱም ይህን ሁኔታ በፍጥነት ለመለወጥና የዲፕሎማቲክ የበላይነቱን (Diplomatic Offensive) ከህወሓት/ኢህአዴግ ወደ ተቃዋሚው ኃይል ለማዞር የሚያስችለን በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ከሁሉ ነገር ቅድሚያ የምንሰጠዉ ጉዳይ ነዉ።

የዲፕሎማቲክ የበላይነት በአንድ ወይንም በሁለት ድርጅት ትግል የሚገኝ፤ ሳይሆን፤ ለጋራ ሃገራዊ ችግሮች፤ ሳያመናቱ፤ የድብቅ ወገናዊ አጀንዳ ሳይዙ፤ በግልጽነት፤ በደፋርነት፤ በቆራጥነት እጅ ለእጅ ተያይዞ እያንዳንዱና ሁሉም በጋራ ለትግሉ የላቀ፤ ተጨባጭ የሆነ አስተዋጾ ማድረግ ሲችል ነው። የእኛ እምነት ይህን ለማድረግ እንችላለን የሚል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግሉ ባለቤት መሆን አለበት ብለን ስለምናምን፤ ለዚህ ጠቃሚ የሚሆን የዲፕሎማቲክ ስትራቴጅ ለመቀየስ ዝግጁ ነን፤ ሌሎችም አብረውን እንዲሰሩ ጥሪያችን እናቀርባለን።

5. <u>የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትና የደህንነት ሃይሎችን በተመለከተ</u>



*Tel.* : +44 7937600756 , +1 9168486790 *E-mail* : shengo.derbiaber@gmail.com

በህወሓት ብቸኛ እዝ የሚመራው የሀገሪቱ መከላከያ ሠራዊትና የደህንነት ሃይሎች አባላት ለህወሓት/ኢህአዴግ ህዝብን የመጨቋኛ መሳሪያ መሆን እንዲያበቁና ከህዝብ ጎን እንዲቆሙ እናሳስባለን።

**ማጠቃለያ**

ከላይ እንዳቀረብነው ሀገሪቱ የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታና የሕዝብ ብሶት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በመገምገም፤ በሀገራችን የተንሰራፋውን አምባገነናዊ ሥርዓት የማስወገድን አስፈላጊነትና ይህንንም ማከናወን ዛሬ የሚታየውን የሃይል አሰላለፍ በማጤን፤ በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩል እስከዛሬ ካለተሟሉት፣ በተለይም ለአንድ አላማ በአንድነት ቆሞ በአንድ ቃል ለመናገር ያለመቻልን፣ የዚህ ጽሁፍ ማዕከሉ ካደረጋቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ በማድረግ ከተነተነ በሁዋላ፤ ሸንጎው ለዚህ ጉዳይ መሟላት ቅድሚያ ሰጥቶ እንደሚሰራ ቃል ገብቷል።

የኢትዮጵያ ህዝብና የተቃዋሚ ኃይሎች ህወሓት/ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በህዝባችን ላይ የሚያደርሰውን ረገጣና ማሰቃየት አክትሞ ለዘላቂ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ የሚበጅ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች ሊያሳትፍ የሚችል፣ ብሄራዊ እርቅንና መግባባትን ግቡ ያደረገ ሂደት እንዲጀምር፤ በግልጽ የሚታወቁትንና የማይታወቁ የሀገሪቱን እስር ቤቶች እያጨናነቁ ያሉ የፖለቲካና የህሊና እስረኞችን ያለቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ፤ ለህዝባችን ተነፍገው ያሉ መሰረታዊ የሰው ልጅ መብቶችን፡- የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር መብቶችን እንዲያከብርና በተግባር እንዲያስፈጽም፤ እነዚህን መብቶች ለማፈን ሆን ተብለው የወጡ አፋኝ የሆኑ ህጎች በሙሉ እንዲሰረዙ፣

የኑሮ ውድነቱ የጎዳዉ ሕብረተሰብ የኑሮ ድጎማ እንዲደረግለት፤ ከፍተኛዉ የዋጋ ግሽበት እንዲቀንስ አስቸኳይ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፣ የፖለቲካ፤ የሲቪክና የሙያ ድርጅቶች በሙሉ፤ ያለምንም ጫና በሰላም ለመሰብሰብ፤ ለመንቀሳቀስ፤ አማራጮችን ለሕዝብ ለማቅረብ እንዲችሉ ለዚህ አመቻች የሆነ ድባብ በአስቸኳይ እንዲፈጥርና ለህብረተሰቡ መንግሥት እንዲያስታውቅ፣

የሚዲያና የብዙሃን መገናኛዎች ለምርጫ ዘመቻ ጊዜ ብቻ ለፐሮፓጋንዳ ተብሎ በሚሰጥ ፍርፋሪ ሰዓት ሳይሆን፣ 365 ቀን 24 ሰዓት ነጻ እንዲሆኑ፤ ተቃዋሚዎች የመንግስት ሚዲያ ተቋማትን የመጠቀም መብታቸው እንዲከበር የሚሉትን መፈክሮች በተገኙ ሚዲያዎች፤ በተቃውሞ ስልፍ በመሳሰሉት ጭምር ሳይታክቱ በየአካባቢው የማጋለጥ ስራ እንዲደረግባቸው ሸንጎዉ ይጠይቃል። ለዚህም የሚያስፈልገዉን ተጋድሎ የሸንጎው አባላት በሚገኙበት አካባቢ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ያሳስባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ አገራችን የእኩልነትና የዴሞክራሲ አገር እንድትሆን በመፈለግ ከላይ የተጠቀሱትን የትግል አቋሞችንና ጥሪዎችን ሲወስድና ሲያቀርብ ከኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጋር በመሆን በአገርቤት ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገር የትግሉ አካልና ግንባር ቀደም መሪ ሆኖ መስዋእትነት መክፈል እንዳለበት ሙሉ በሙሉ በማመን ነዉ። ይህም በጊዜዉ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምን ማድረግ እንደሚገባን የሚገልጽ ዝርዝር አሰራርን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ወደፊት ቀጣይ እርምጃዎቻችንን ለሕዝባችን በየጊዜዉ የምናወጣ መሆናችንንና ሕዝባችንም በመከታተል በትግሉ ሙሉ ተሳትፎ እን ዲያደርግ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ!

አፋኝ የሆኑ የሚድያና የሽብርተኞች ህጎች በሙሉ ይሰረዙ!

የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ድርጅቶችና የሙያ ድርጅቶች ያለምንም ጫና በሰላም ለመሰብሰብ፤ ለመንቀሳቀስ፤ አማራጮችን ለሕዝብ ለማቀረብ እንዲችሉ ለዚህ አመቻች የሆነ ድባብ በአስቸኳይ ይፈጠር!

የሚዲያና የብዙሃን መገናኛ አካላት ነጻነት ያለገደብ ይፈቀድ፣ ተቃዋሚዎች የመንግስት ሚዲያ ተቋማትን የመጠቀም መብታቸው ይከበር!

ለሰላም፣ እርቅና ዴሞክራሲ የሽግግር ሂደት ግንባታ ሁሉን አቀፍ አገራዊ ጉባኤ በአስቸኳይ ይጠራ!

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ( ሸንጎ)

ታህሳስ 1፣ 2005 (December 10, 2012)



*Tel.* : +44 7937600756 , +1 9168486790 *E-mail* : **shengo.derbiaber@gmail.com**